# አሥራ ሁለተኛ ትምህርት ከመጋቢት 9 — 15 Mar 18—24

## የመንፈስ ቅዱስ ሥራ

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ዩሀ 16:8-11; ሮሜ. 5:10; ዕብ. 4:15, 16; 1 ጴጥ. 5:8, 9; 1 ዩሀ 5:12, 13; መዝ. 31:24.

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡- "በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ፤ ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተስፋ ተትረፍርፎ እንዲፈስላችሁ ነው።።" (ሮሜ 15:13)።**

በመንፈስ ቅዱስና መንፈሳዊነት ርዕሰ ጉዳይ ላይ ስናጠና የነበረውን ትምህርት እየቋጨን ባለንበት በዚህ ወቅት፤ ገና ትኩረታችንን ባላገኘ አንድ ሌላ ወሳኝ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ላይ ምልከታ እናደርጋለን።

የሱስ ወደ አብ እንደሚሄድ ለደቀ መዛሙርቱ ባስታወቀበት ወቅት መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። "አብ በስሜ የሚልከው አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ ግን ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኳችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል" (ዮሐ. 14:26)።

የሱስ እንደ ተናገረው "የሚረዳ"፣ "አጽናኝ" ወይም "ጠበቃ" የሚል ስያሜ የተሰጠው መንፈስ ቅዱስ--ስለ እኛ የሚማልደው ጰራቅሊጦስ ነው። ይህ የመማለድ ሥራ ዓለምን ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ "በመውቀስ" ገቢራዊ እንደሚሆን የሱስ አስታውቆአል (ዮሐ. 16:8)።

በዚህ የመጨረሻ ሳምንት፤ ይህን የተለየ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዝርዝር ለማጥናት እንሞክራለን። በተጨማሪ ይህ የመንፈስ ሥራ ከሌሎች ከሁለት የአገልግሎቱ ክፍሎች--ማለትም ከተረጋገጠው ደኅንነታችንና የየሱስ ደቀ መዛሙርት እንድንሆን ከሚያነሳሳን የተባረከ ተስፋ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ እናጠናለን፤።

*እሑድ መጋቢት 10* *Mar 19*

### ስለ ኃጢአት መውቀስ

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- ዮሐ. 16:8-9። መንፈስ ቅዱስ ለእኛ የሚሠራው አንገብጋቢ ሥራ ምንድን ነው? ጉዳዩን ያን ያህል አስፈላጊ ያደረገውስ ምንድን ነው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የሱስ--ጰራቅሊጦስ በማለት መንፈስ ቅዱስን የጠራበት ቃል--ረዳት፣ ጠበቃ እና አጽናኝ የሚሉ ጥልቅ ጽንሰ ሃሳቦችን ይዞአል፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወንድሞች ከሳሽ ወይም እንደ አቃቤ ሕግ ሆኖ ወደዚህ አስፈላጊ የመውቀስ አገልግሎት አይገባም፡፡ እርሱ በየሱስ የተላከው እንዲኮንነን ሳይሆን ነገር ግን በብርቱ የሚያስፈልገንን ጸጋ መመልከት እንችል ዘንድ እንዲረዳን ነው፡፡

ማጽናናት የሚችለው ብቻ--እርዳታው ስለሚታመን ተቀባይነት ማግኘት ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ ብዙ የሚጠበቅባው ክርስቲያኖች ኃጢአተኞችን ሲቀርቡ--ለመርዳት የተዘጋጀ የተሰበረ መንፈስ ሳይሆን ነገር ግን ለመክሰስ የቸኮለ ስብዕና ማሳየታቸው አሳዛኝ ነው፡፡ በዙሪያችን ያሉ ወገኖችን ኃጢአት እያነፈነፍን ለሌሎች መጠቋቆሚያ የምናደርጋቸው ከሆነ--በየሱስ ያልተጠራንበትን ነገር እያደረግን ነው፡፡ ኃጢአተኞች ሆነን፤ የሌላውን ጉድፍ ነቅሰን አደባባይ የምናወጣ--ለመሆኑ ራሳችን ማን ነን?

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ሮሜ 2፡1፣ ማቴ. 7፡3፡፡ ከጥቅሶቹ ልንወስድ የሚገባው መልእክት ምንድን ነው?

እኛ የእርሱ ምስክሮች እንጂ የዐቃቤ ሕግ ሥራ የምንሠራ ከሳሾች አይደለንም፡፡ የተጠራነው ለሰብዓዊው ፍጡር ቤዛ ለሆነው ኃይል ምስክር ለመሆን እንጂ ሌሎችን በጥፋታቸው ልንኮንን አይደለም፡፡ ሌሎችን በኃጢአታቸው ልንወቅሳቸው ስንሞክር የእኛ ያልሆነውን አገልግሎት እየወሰድን ነው--ስለ ኃጢአት የመውቀስ ኃላፊነት የመንፈስ ቅዱስ ነውና!

ዓለምን ስለ ኃጢአት “ይወቅሳል” (ዮሐ. 16፡8) የሚል ኃላፊነት የተሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንጂ እኛ አይደለንም፡፡ ሕይወታቸው በየሱስ እንዲመራ ያልፈቀዱ ሰዎች በትክክል ኃጢአት ምን ማለት እንደሆነ ወይም አውዳሚ ኃይሉን በተጨባጭ የሚያስተውል ስሜት የላቸውም፡፡

እዚህ ላይ የተቀመጠው ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ የተወሰኑ የተሳሳቱ ድርጊቶችን ነቅሶ ያወጣል የሚል አይደለም፡፡ ይልቁንም የሁሉም ኃጢአቶች መሰረት ወደ ሆነው የሚያመራ ሲሆን--ይኸውም በየሱስ ክርስቶስ አለማመን ነው (ዮሐ. 16፡9)፡፡ ሰብዓዊውን ፍጡር በጥልቅ የሚሰማው ሥቃይና ባይተዋርነት መንስኤ፤ እግዚአብሔር ከምንገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ ሊታደገን የላከልንን መንፈስ በመቀበል ፋንታ--ከእርሱ መራቃችንና እምቢተኝነት ማሳየታችን ነው፡፡

የሁሉም ኃጢአት መሰረታዊ ችግር በየሱስ አለማመናችንና ከኃጢአትና ከጥፋተኝነት ስሜት ሊያድነን የሚችለውን እርሱን መቃወማችን ነው፡፡ እኔነትን የሁሉም ነገሮች ማዕከል አድርጎ የሚያኖረውና የእግዚአብሔርን ቃል ለማመን አሻፈረኝ ባዩ ይኸው ኃጢአት ነው፡፡ ስለ እኛ በሞተው በክርስቶስ የምናገኘውን--አጥብቆ ለሚያስፈልገን ንስሐና የተዋጀ ሕይወት ልባችንንና አእምሮአችንን መክፍት የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡

*ሰኞ    መጋቢት 11*                                                                                    *Mar 20*

## የክርስቶስ ጽድቅ የሚያስፈልገን ስለ መሆኑ

መንፈስ ቅዱስ ዓለምን የሚወቅሰው ስለ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ስለ ጽድቅም ጭምር መሆኑን ዮሐ. 16፡8 ይነገረናል፡፡ በሌላ አነጋገር ይህ ዓለም የኃጢአትን ምንነት ብቻ ሳይሆን ጽድቅንም እንዲሁ በትክክል አያውቅም፡፡

ያልተለወጡ ሰዎች--ውጪያዊው በጎ ሥነ ምግባር በቂ እንደሆነ ያስባሉ። የእነርሱ ምኞት አምላካዊውን ጽድቅ ያማከለ ሳይሆን ነገር ግን በግላዊው ጽድቅ ስር የዋለ ነው። ለአምላካዊው ሕግ ታዛዥነትን ለማሳየት የመሻት ዓይነት--ውጪያዊውን ድርጊታቸውን ተከትሎ የሚመጣውን ጽድቅ ይመኛሉ። ሆኖም ሕጉን ለመታዘዝ መሞከራችን በእግዚብሔር ፊት ጻድቅ አያደርገንም።

ኢሳይያስ በእርሱ ዘመን ይስተዋል የነበረውን ግላዊነትን (እኔነትን) ማዕከል አድርጎ የነበረውን የጽድቅ ሥራ "የመርገም ጨርቅ" (ኢሳ. 64፡6) በማለት ይገልጸዋል። ግላዊነት--መነሳሻ መንስኤ የሆነው ምርጥ ኃይማኖተኝነትም እንዲሁ የጽድቅን ተቃራኒን ፍቺ ይይዛል።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕግ የሚጠይቀውን ሁሉ የሚያሟላው የየሱስ ጽድቅ ለሁላችንም በቂ ነው። በእግዚአብሔር አብ ፊት ስለ እኛ የሚቆጠርልንን ይህን ጽድቅ በየሱስ ክርስቶስ ላይ በሚኖረን እምነት ብቻ የግላችን ማድረግ እንችላለን።

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡- ሮሜ 5፡10፣ ዕብ. 4፡15-16። ጽድቃችን ክርስቶስ በአብ ፊት በሰማይ ከሚሰጠው ሕያው አገልግሎት ጋር ተዛምዶ ሊኖረው የቻለው እንዴት ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ሕጉ የሚጠይቀው ማንኛውም የጽድቅ ሥራ ፍጹም በሆነው በየሱስ ሕይወት ፍጻሜ አግኝቶአል። እነሆ እርሱ ስለ እኛ ሞተ። ምንም እንኳ በምድራዊ ሕይወቱ ሰዎች ተቃውመውትና ነቅፈውት በመጨረሻም ለሞት ቢያበቁትም--ሰማያዊው አባት ግን በደስታ ተቀበለው። የየሱስ ቤዛነትና የመዋጀት ሥራ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ማግኘቱ እነሆ በትንሳኤው ተገልጦ መታየት ቻለ። እኛ ደኅንነት ሊያስገኝልን የሚችል የጽድቅ ሥራ ስለሌለን--የጽድቅ ሞቱ ስለ እኛ ይቆጠር ዘንድ የሱስ አሁን በሰማይ እየማለደልን ይገኛል (ዕብ. 4፡15-16)።

እርሱ በእኛ ውስጥ ስለሚኖር እኛም መኖር እንችላለን። "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ፤ ከእንግዲህ እኔ አልኖርም፤ ነገር ግን ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖረው ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን አሳልፎ በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ እምነት ነው" (ገላ. 2:20)። የሱስ በእኛ ውስጥ ሲኖር በመንፈስ እንመላለሳለን (ሮሜ 8፡4)፤ በመንፈስም ኃይል አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት እንቀበላለን (ገላ. 3:2-5፣ 5:16፣ 18)።

የየሱስ በአብ ፊት መክበር በመንፈስ አማካኝነት ከእኛ ጋር መሆኑን ያመላክታል። በመንፈስ ኃይል የተሞሉት ደቀ መዛሙርት--ከክርስቶስ ጋር ስምሙ የነበረው ሕይወታቸው በየጊዜው እያደገ ይሄድ ነበር።

ትእዛዛቱን በራስዎ ለመጠበቅ የመሞከርዎ--የራስዎ ጽድቅ ምን ያህል የረከሰ እንደ ሆነ በተጨባጭ መለማመድ ችለዋል? በግላዊው ፋንታ የክርስቶስ ጽድቅ ምን ያህል እንደሚያስፈልግዎ ይህ ምን ያስተምሮታል?

*ማክሰኞ　　መጋቢት 12*　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　　*Mar 21*

## ስለ ፍርድ መውቀስ

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ዮሐ. 16፡8፣11። የሱስ ስለ ምን ዓይነት ፍርድ እየተናገረ ነው? ይህ ፍርድ መልካም የምስራች የሆነው ለምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የመንፈስ ሥራ አካል የሆነ አንድ የመጨረሻ ወቀሳ የሚቀር ሲሆን ይኸውም ዓለምን ስለ ፍርድ የመውቀሱ እውነታ ነው፡፡ በዚህ ጥቅስ ዙሪያ የምንሰጠው አብዛኛው ስብከት የተሳሳተና ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ዓይነት ነው፡፡ ስለ ኃጢአትና ስለ ጽድቅ በሚሉት ሃሳቦች ላይ በሚደረጉ ውይይቶች--የጽድቅ በእምነትን አስተምህሮ የተቀበሉ ክርስቲያኖች፤ ክርስቶስን ለመቀበል የሚቃወሙትን ለማስጠንቀቅና ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ለመናገር አዘውትረው ሲጠቀሙበት ይታያል፡፡ ይህን መልእክት ሲያቀርቡ ብዙውን ጊዜ ፍርሐት የሚለቅ ዓይነት ድምጸት በመጠቀም ኃጢአተኞች ስለሚጠብቃቸው ፍርድ ለማስጠንቀቅ ይፈልጋሉ፡፡

የፍርድ መኖር ተጨባጭ ሐቅ ቢሆንም ነገር ግን በዮሐ. 16፡11 የሱስ የሚናገረው ይህን አይደለም፡፡ ጌታ በዮሐ. 12፡48 ከተናገረው ጋር በተመሳሳይ ወደ ፊት ስለሚሰጠው ፍርድ እየተናገረ አለመሆኑ ራሱ ቋንቋው ሊመራን ይችላል፡፡ በመሆኑም የሱስ በዚህ ጥቅስ እየተናገረ ያለው የፍርድ ገጽታ ሰይጣን በቀራኒዮ እንደ ተፈረደበት የሚያመላክት መልካም የምስራች ነው፡፡ ቀንደኛው የእውነት ጠላት ዲያብሎስ ዛሬ እየኖረ ያለው በተውሶ ዘመን ውስጥ ነው፡፡ ፍርድ ጊዜውን ጠብቆ ገቢራዊ ይሆናል፡፡ ሆኖም መልእክቱ የዚህ ዓለም ገዢ ተፈርዶበታል--ፋይሉም ተዘግቶአል! የሚል አንደምታ አለው (ዮሐ. 12፡31)፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- 1ጴጥ. 5፡8-9፡፡ ጴጥሮስ ሰይጣንን የገለጸበት መንገድ ምን ይመስላል? ልንቃወመው የምንችለው እንዴት ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ዲያብሎስ በቀራኒዮ ክፉኛ ሽንፈት ቢደርስበትም፣ የቀረው ጊዜ አጭር ቢሆንም ነገር ግን ዛሬም በዚህ ምድር አለ፡፡ ሰዎችን በተቻለው የምርኮው ሰለባ ለማድረግ በቁጣ የሚውጠውን ፍለጋ ወዲህ ወዲያ እየተዟዟረ ይገኛል፡፡ ሆኖም ዲያብሎስ የተሸነፈ ጠላት ነው፡፡ የሱስ የድሉ ባለቤት ሆኖአል፡፡ የየሱስ ደም በእርግጥም ነጻ አውጥቶናል፡፡

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የኅብረ ብሔሩ ጦር እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ሰኔ 6/1944 ፈረንሳይን ተቆጣጥረው በነበሩት የናዚ ወታደሮች ላይ ወሳኝ ጥቃት ሲፈጽም ናዚዎች ለውድቀታቸው መንስኤ የሆነ ከባድ ሽንፈት ደረሰባቸው፡፡ ሆኖም የኅብረ ብሔሩ ጦር ጥቃት በጀመረበትና ጦርነቱን በድል ባጠናቀቀበት ጊዜ (ግንቦት 8/1945) መሃል የነበሩት 11 ወራቶች--የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እጅግ የከፉትና ብዙ ሕዝብ ያለቀባቸው ነበሩ፡፡ በተመሳሳይ ሰይጣን በመስቀል ላይ ክፉኛ መሸነፉን ያውቃል፡፡ ሆኖም ውጊያውን በመንቻካነት በመቀጠል የሚችለውን ያህል ለመዋጥ እየሠራ ይገኛል፡፡ በእነዚህ ፈታኝ ጊዜያቶች ራሳችንን ተቆጣጥረን በንቃት እየተመላለስን ጭንቀታችንን ሁሉ ለእኛ በሚጠነቀቅልን በየሱስ ላይ እንድንጥል ተጠርተናል (1ጴጥ. 5፡7-8)፡፡

ፍርድ መልካም የምስራች የሆነበት ምክንያቱ ምንድን ነው? በፍርድ ወቅት የተረጋገጠው ተስፋችን ማን ነው? ሰዎችን በፍርሃት ድባብ ውስጥ በሚከት ዓይነት ሳይሆን ነገር ግን ተስፋን በልባቸው በሚያሰርጽ መልኩ ስለ ፍርድ መናገር የምንችለው እንዴት ነው?

## የተረጋገጠው የደኅንነት ተስፋ

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- 1 ዮሐ. 5:12- 13፣ ሮሜ 8:15-17፣ 2ቆሮ. 5:5፡፡ ክርስቶስን አንዴ የግል አዳኛችን አድርገን አድርገን ስንቀበል የዘላለማዊ ህይወት ማረጋገጫ ሊኖረን የቻለው ለምንድን ነው? የዚህ የተረጋገጠ ተስፋ መሰረቱ ምንድን ነው?**

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኞችን ወደ የሱስ የመምራት ሥራ ይሠራል፡፡ የየሱስ በእኛ ምትክ መሞት ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ እንድንፈጥር አስችሎናል፡፡ በየሱስ ያገኘነው አዲስ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ልጆች አዲስ ሕይወት የመኖር ነጻነት አጎናጽፎናል፡፡ የእግዚአብሔር ጠላት መሆናችን አክትሞ (ሮሜ 5:10) እንደ ሥጋ ፈቃድ ሳይሆን ነገር ግን በመንፈስ የምንመላለስ (ሮሜ 8:4) አስተሳሰባችንም ለመንፈሳዊ ነገሮች ትኩረት የሚሰጥ ሆኖአል (ሮሜ 8:5)፡፡ የክርቶስ መንፈስ ባይኖረን ኖሮ ልጆቹ ባልሆንን፣ የእርሱ ተብለን መጠራትም ባልቻልን ነበር (ሮሜ 8:9)፡፡ አሁን ግን በውስጣችን የሚኖር የመንፈስ ምስክር አለን፡፡ ይህ መንፈስ የየሱስ መሆናችንንና ከክርስቶስ ጋር የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች መሆናችንን ይመሰክርልናል (ሮሜ 8:17)፡፡ የሱስን ከሙታን ያስነሳው ያው መንፈስ በመንፈስ ሟች በነበርነው--አሁን በእኛ ውስጥ ስለሚሠራና እኛንም ስለሚያበጀን ሕያው ያደርገናል (ሮሜ 8:10)፡፡ ከዚያ በላይ--በእውነት የእግዚአብሔር የመሆናችንን ማረጋገጫ በልባችን ያትማል፡፡ የደኅንነታችንን የወንጌል የምስራች በመስማታችንና አምነን በመቀበላችን ተስፋ ሆኖ ከተሰጠው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በየሱስ ታትመናል (ኤፌ. 1:13-14)፡፡ እያንዳንዱ አማኝ ይህ የተረጋገጠ ተስፋ ይኖረዋል (1ዮሐ. 5:12-13)፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ኤፌ. 1:13-14፡፡ በመንፈስ ማኅተም መታተም--ምን ማለት ነው?**

ክርስቶስን የተቀበሉ ከመንፈስ በመወለዳቸው (ዮሐ. 3:3፣ 5) የአዲስ ልደት ባለቤቶች ሆነዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ይህን እውነት በልባችን ስለሚያትመው የመዳናችንን ማረጋገጫና የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን የምናገኘው ደስታ ተሞክሮ ባለቤት እንሆናለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ንብረትነት ያውቀናል፡፡ "ማንም የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው፣ እርሱ የክርስቶስ አይደለም" (ሮሜ 8:9)፡፡ እንዲህ ሲሆን እግዚአብሔር አፍቃሪ አባታችን--እኛም ልጆቹ መሆናችንን አእምሮአችን በተሻለ ማስተዋል ይጀምራል፡፡ መንፈስ ቅዱስ የሱስ ዳግም ሲገለጥ በስተመጨረሻ ለምንቀበለው የዘላለማዊ ሕይወት ስጦታ (1ቆሮ. 15:51-54) ቀብድ፣ መያዣ ወይም መተማመኛችን ነው፡፡ ይህ እንግዲህ ትክክለኝነቱ የተረጋገጠ የአስተማማኝ እምነት ማኅተም ነው፡፡ ክርስቲያኖች ይህ የተረጋገጠ ተስፋ ሳይኖራቸው ሌሎችን ሊያሳምን በሚችል ኃይል ምስክር ሲሆኑ ለመመለክት አዳጋች ይሆናል፡፡

"በወኔ ሲናገሩ፣ ድምጽዎን በእምነትና በተስፋ ከፍ አድርገው ሲያሰሙ--ሁለመናዎ በጌታ ብርሃን የተሞላ ይሆናል፡፡ ማንም ሰው ሊዘጋው ስለ ማይችለው--ክርስቶስ በፊትዎ ወለል አድርጎ ስለ ከፈተው በር ለአፍታ እንኳ ማሰብዎን አያቁሙ፡፡ እድሉን የሚሰጡት ከሆነ እግዚአብሔር ማንኛውም እኩይ ሾልኮ ሊገባ የሚችልበትን ቀዳዳ ጥርቅም አድርጎ ይዘጋሎታል፡፡ ጠላት እንደ ጎርፍ እያጓራ ቢመጣ መክተው ማቆም የሚችሉበትን አምላካዊ ቃል የጌታ መንፈስ ስለ እርስዎ ከፍ ያደርጋል፡፡"–Ellen G. White, The Advent Review and Sabbath Her-ald, April 16, 1889.

## መንፈስ ቅዱስና ተስፋ

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ሮሜ 5:4- 5፣ 15:13፣ 1ቆሮ. 13:13። ፍቅርና ተስፋ እርስ በርሳቸው መተሳሰር የቻሉት እንዴት ነው? መንፈስ ቅዱስ ፍቅርና ተስፋን ለእኛ የሚሰጥ መሣሪያ መሆን የቻለው እንዴት ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን ማህደር ያፈሰሰው መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንድንፈጥር በማስቻል ፍቅሩ በውስጣችን እንዲኖር ያደርጋል። ጽኑው፣ የማያወላውለውና የማይለወጠው የእግዚአብሔር ፍቅር የተስፋችን መንስኤና ጠንካራ መሰረት ነው። ያለ ፍቅር አንዳችም ተስፋ ሊኖር አይችልም። ፍቅር ብቻ ተስፋን ያፈልቃል። ፍቅሩ ከታማኝነቱ ጋር የተሳሰረው ይህ አምላክ ዳግም ተገልጦ እርሱ ወዳለበት ይወስደናል የሚል ግሩም ተስፋ አለን።

ጥቅሱን ያንብቡ፡-- መዝ. 31:24። ተስፋ በእኛ ላይ ምን ዓይነት ውጤቶች አሉት?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ተስፋ ልብን የማሞቅና የማነሳሳት ኃይል አለው። ተስፋ አዲስ ጉልበት ይሰጣል። ተስፋ እንድንዘምርና ሐሴት እንድናደርግ ያስችለናል። ተስፋ በጣም አስፈላጊ የሕይወት ቅመም ነው። ተስፋ ባይኖር የሕይወት ዓላማ ምን ሊመስል ይችል ይሆን?

ተስፋ ማድረግ--መልካም የሆነው ወይም ቀናው ብቻ ይደርሳል ብሎ ከሚጠባበቀው አስተሳሰብ ጋር አንድ አይደለም። መልካም የሆነው ብቻ ገቢራዊ ይሆናል ብሎ የሚጠባበቀው አስተሳሰብ--የአየሩ ጸባይ፣ ምጣኔ ሐብቱ፣ የክፍል ደረጃው፣ ገቢው…--ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል ብሎ ያምናል። በተቃራኒው ተስፋ እንዲህ ያለውን ጭፍን አመለካከት አይጋራም። ይልቁንም በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ እና ቀደም ባሉት ጊዜያቶች በሰጠው ተስፋዎች ላይ መሰረት ያደረገ ነው። ተስፋ--እግዚአብሔር ታማኝና እውነተኛ በመሆኑ የተናገረውን በተግባር ይገልጠዋል ብሎ ያምናል። እግዚአብሔር ሊተማመኑበት የሚገባ አምላክ እንጂ--ወለም ዘለምን የማያውቅ መሆኑን በተጨባጭ አስመስክሮአል። ጽኑነቱና እውነተኝነቱ የተስፋችን መሰረቶች ናቸው።

ደግሞም የተስፋችን መሰረት የተሰቀለው የሱስ መሆኑ አያጠያይቅም። ወደ መስቀሉ ቀና ስንል እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር በተጨባጭ የገለጠበትን ኃያል ትዕይንት እንመለከታለን። የሱስ ስለ ኃጢአታችን የሞተበት መስቀሉ--እግዚአብሔር ወደር የማይገኝለት አምላክ የመሆኑን እውነት ለእኛም ሆነ ለዩኒቨርስ ገልጦ ያሳያል። ምንም እንኳ እጅግ ግዙፍ በሆነው ዩኒቨርስ በእንግድነት የምንኖር፣ የወደቅን ፍጥረቶች ብንሆንም ተስፋ ማድረግ ግን እንችላለን። ተስፋችን ራሳችን ወይም የሠራነው "ታላቅ" የተባለ ነገር ሳይሆን ነገር ግን ራሱን በመስቀል የገለጠልን አምላካችን ነው።

የአድቬንቲስቶች ተስፋ በእግዚአብሔር ታማኝ ኪዳን ላይ የተመሰረተው እንዴት ነው? ተስፋ በሕይወታችን ላይ ተጽእኖ የሚኖረው እንዴት ነው? በተስፋ መቁረጥ ፋንታ ተስፋ የማድረግን በዕለት ከዕለት ሕይወታችን ማጎልበት የምንችለው እንዴት ነው?

## ተጨማሪ ሃሳብ:-

ተጨማሪ ሃሳብ፡- Read selections of Ellen G. White, Ye Shall Receive Power, especially the October section “Ready for the Spirit.”

*መንፈስ ቅዱስ ደኅንነታችንን ወደ ክንውን ለማምጣት ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዚአብሔር ወልድ ጋር በውህደት ይሠራል በሚል ሥራውን በአጭሩ ማስቀመጥ እንችላለን፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከመንፈሳዊ ሞት ይቀሰቅሰናል፡፡ ኃጢአተኝነታችንን እንድንገነዘብ በመምራት ውስጣችንም ሆነ ውጪያችን የጠፋ መሆኑን በተጨባጭ እንድንመለከት ዐይኖቻችንን ይከፍታል፡፡ የተለወጠ ሕይወት ምኞት በውስጣችን በመለኮስ ውስጣዊው ማንነታችን አጥብቆ ለሚያሻው ነገር ባለ መፍትሔ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ይመራናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ ወደ የሱስና እርሱ ወዳደረገልን ነገሮች እያመላከተን የተረጋገጠውን ተስፋ ይሰጠናል፡፡ አብልጠን የሱስን እንድንመስል ከእርሱ ጋር ስምሙ ያደርገናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በታማኝነት እንድንኀዝ ይረዳናል፡፡ አምላካዊውን ፈቃድ መፈጸም እንድንችልና ውጤታማ አገልግሎት እንድንሰጥ ያስችለናል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ--የክርስቲያናዊ ሕይወታችንና የኃይማኖታዊ አስተምህሮአችን ብቸኛ መመሪያ እንዲሆን ይሠራል፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ የት ልንሆን እንችል ነበር? ምን ማድረግስ እንችል ነበር? ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ማቅረብ የተሳነን፣ ደስታ የራቀንና የጠፋን በሆንን ነበር፡፡ የሱስ መንፈስን እንደሚልክልን ቃል ስለገባልንና ስለላከልን ምስጋና ይድረሰው፡፡ “መንፈስ ቅዱስ ሕዝቡ ሐሴት እንዲያደርግ የሱስ አባቱን ሊጠይቅ ከሚችለው ስጦታዎች ሁሉ የላቀውና እጅግ ከፍተኛው ነበር፡፡”–* Ellen G. White, Ye Shall Receive Power, p. 13.

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

- *ኃጢአት ምንድን ነው? ጽድቅስ?--በሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች ዙሪያ ምልከታ ያድርጉ፡፡ እኛ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል የምናምን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን የማይቀበሉ በኃጢአትና በጽድቅ ዙሪያ ካላቸው እሳቤ የተለየ አመለካከት የኖረን ለምንድን ነው? በእኛና በእነርሱ መካከል ያሉት ልዩነቶች ምንድን ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎቹ ምንጮች ስለሌሏቸው--ስለ ኃጢአትና ስለ ጽድቅ የሚያስተምረን ትምህርት ምንድን ነው?*
- *ከመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች መሃል ለእርስዎ የበለጠ ዋጋ ያለው የትኛው ክፍል እንደሆነ ለሰንበት ትምህርት ጥናት አባላት ያካፍሉ፡፡ ይህ ለእርስዎ በተለየ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? ሕይወትዎ ላይ ያሳረፈው ተጽእኖስ ምን ይመስላል?*
- *በየሱስ ስላለን ተስፋ ለሰንበት ትምህርት ጥናት አባላት ይናገሩ፡፡ የዚህ ተስፋ ባለቤቶች እንድንሆን መንስኤ የሆኑት ነገሮች ምንድን ናቸው? ማለትም--ምናልባት አንድ ሰው ተስፋ ሊያደርጉ የቻሉበትን ምክንያት* (1ጴጥ. 3:15) *ቢጠይቆት ምላሽዎ ምን ይሆናል? የሚሰነዝሩት ሃሳብ ምን ያህል አሳማኝ ነው?*

- በዚህ ሳምንት--በተረጋገጠው ደኅንነት ዙሪያ ሊነሱ በሚችሉ ጥያቄዎች ላይ ተነጋግረናል፡፡ የመዳን ማረጋገጫው ምንድን ነው? ይህ ማረጋገጫ ያለን ከሆነ--ለምን ሊኖረን ቻለ? ይህ ደኅንነት በምን ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይገባል? ግምታዊ ከሆነው አስተሳሰብስ በምን ይለያል?